በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ማሻሻያ

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣው መመሪያ ቁጥር ፸፯/፪ሺ፬ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል::

አንቀጽ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፫ ተተክቷል::

፫. ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት ዋጋ

፩. ወኪሉ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ዋጋ ያለው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈፀም የሚችለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ብቻ ነው::

፪. ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) በላይ ሲሆን፣ ወኪሉ ታክሱን ቀንሶ ማስቀረት ይኖርበታል::

Directive Lether./GT

፫. ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈለው ክፍያ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) እና ከዚያ በታች ከሆነ ወኪሉ የታክሱን ሂሳብ ጭምር ለታክስ ከፋዩ መክፈል ይኖርበታል። ታክስ ከፋዩ በዚህ ዓይነት የሰበሰበውን ታክስ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፬. በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ወይም ድርጅት የሚቀርብ ዕቃ ወይም የሚሰጥ አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ በግዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ በተደነገገው መሠረት ይመራል።

፫. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከሰኔ ፭ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

